# «ሚሌንየሙ ሲከበር»





...በሶማሊያ የደም ዋጋ - ባሜሪካን ዶላር ጉርሻ፣
ባላሙዲን ውስኪ ቅጂ - በወያኔ ጥጋብ ቅርሻ፣
በልመና ስንዴ ቂጣ - በ«ወርልድ ባንክ» ውዝፍ ብድር፣
«እልል እንበል?» ወይስ እ-------ሪ! - ሚሌኒየሙ ሲከበር::

... ለአገር ሲል፣ ለሕዝብ ሲል - ድምጹን ሰጥቶ ያስቆጠረው፣
ባረመኔው የግፍ ጥይት - በግንባሩ የተደፋው፣
ደሙ ሳይደርቅ በዚያች ምድር - በላዩ ላይ ሲጨፈር፣
ምን ይል ይሆን? ህሊናችን - ሚሌንየሙ ሲከበር::





... ስንቱ ወጣት... ስንቱ ምሁር፣
የሕዝብ ኩራት ያገር አድባር...፣
የለውጥ ዓርማ ሻማ ሆኖ፣
ወህኒ አምባ ተከርችሞ፤
ልንደንስ ልንጨፈር?
ሚሌንየሙ ሲከበር?!

ሰላም-አልባ፣ ፍቅር-አልባ፣ ምግብ-አልባ...፣
መተሳሰብ፣ መተማመን፣ ዴሞክራሲ...፣
ብልጽግናን... ሳንገነባ፤
ዘመን ቆጥረን የዕድሜ ሽበት፣
ሳንንፏቀቅ ካለንበት...፣
ሐቅን ክደን ትቢት ወርሰን፣
ተስፋን ቀብረን ብረት ታቅፈን፣
ብንሽቅጥ ብናምታታ፣
የረገበ ከበሮችንን ሽቅብ ዘለን ብንመታ፣
ችጋር፣ ጠኔ አንፈራፍሮን፣
ላለም ታይታ ሃፍረት ሆኖን፣
ብንወሻክት፣ ብንቀባጥር፣
ብንሽመጥጥ... አንገት ደፍተን፣
ምፀት እንጂ ምን ሊባል ነው?
በራስ ዕድሜ፣ ባገር ዕድሜ...
በትውልዱ የመቀለድ፣
ሆዳችን ሲያውቅ ዶሮ ማታ...
ፅልመት ኑሮ፣ መራር ኮሶ ተግተን ግድ፤
አበስኩ ገበርኩ! የኛ ነገር፤
ሚሌንየሙ ሲከበር::





ታሪክ ይፍረድ! ጊዜ ይመስክር!
እንዴት... እንዴት... እንደነበር፤
በምስኪኗ እናት ምድር፣
ሚሌንየሙ ሲከበር!





ጌታቸው አበራ
ሰኔ 1999 ዓ.ም (2007)